# ድርጅት አልባ ትግል ከንቱ ልፋት ነው

ከተመክሮአችን ትምህርት ቀስምን፣አወቅን፤ ካለፈው ተማርን፣ታረምን ብለን ልንነሳ ስንል የአዋቂ አጥፊዎችና በአብዛቅሮው ደግሞ የገዢው ቡድን መሰሪ ተላላኪዎች የሕዝብን የመደራጀት አስፈላጊነት አቃለው ከማቅረብ አልፈው በድርጅቶች ላይ አፀያፊ ዘመቻቸውን ይከፍታሉ፡፡ አረመኔው አገዛዝ የፈፀመውንና የሚፈፅመውን ግፍ ሁሉ በድርጅቶች ጥፋት መድበው ድርጅቶችን ይወነጅላሉ፤ ያጥላላሉ፡፡ ደፈር ያሉት የፖለቲካ መሀይሞች ወይም የወያኔ ቅጥረኞች ደግሞ ሕዝብ ለመታገል ድርጅቶች አያስፈልጉትም፤ ራሱ በራሱ ይነቃነቅ የሚል መርዘኛ ሰበካቸውን ይረጫሉ፡፡ የድርጅት አስፈላጊነትን የሚያስረዱ ወይም ድርጅታችን በግርግር አይፈርስም ወይም ተጣማሪ ተቀናጀ በሚል በተልፈሰፈሰ ስብስብ ገብቶ አይሰጥምም፣አይጠፋም ያሉትንም ድርጅታቸውን አስቀደሙ በሚል መክሰሱ የወቅቱ ጫጫታ ሆኗል፡፡

የድርጅት አባላት የድርጅታቸውን ህልወና መንከባከባቸው የሚጠበቅና መሆንም ያለበት ነው፡፡ ድርጅትን አሰቀደሙ ክስ ብዙውን ጊዜ የሚደመጠው ድርጅት መመስራትና መገንባት ካቃታቸው ነው፡፡ የሆነ ድርጅት አባላት ድርጅታቸውን የሚወዱትና የሚንከባከቡት አቅዋሙ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ በመሆኑና ድርጅቱም የትግል መሳሪያ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ እምነት ለምሳሌ የኢሕአፓ አባላት ለድርጅታ ቸው ያላቸውን ፍቅር ይገልጣል፡፡ የኢሕአፓ አባላት ድርጅታቸው ለቆሙለት ሕዝ ባዊ አላማ ይታገሉ ዘንድ ያገለገላቸውና እየሰራላቸውም ያለ በመሆኑ ይወዱታል፤ ከጥቃት ይጠብቁታል፡፡ ይህ የድርጅት ፍቅር ከሀገር ፍቅር ጋር የተቀረኛ እንጂ የተፃረረ አይደለም፡፡ ኢሕአፓን ወዶ ኢትዮጵያን መጥላት፣ኢትዮጵያን ወዶ ኢሕአፓን መጥላት የሚታሰባቸውም ሊሆን አልቻለም፣አይችልምም፡፡ ለኢትዮጵያ ጠላቶች ያደሩ ግን ይህን አታጋይ ድርጅት አምርረው ስለሚጠሉም ህልውናው በዚህም በዚያም ሰበብ እንዲጠፋ ይጥራሉ፡፡ በስድብና ክስ ዘመቻ ሊያሰምጡት ጥረ ው ሲከሽፉ ወዳጅ መስለው ተጠግተው በትብብር ሽፋን ማንነቱን ሰርዘው ሊያሽ መደምዱትም ሞክረዋል፡፡ ግን አልተሳካላቸውም፡፡

ከዚሁ በተያያዘ እየተስተጋባ ያለው ዘመቻ ደግሞ ድርጅቶች ለድል ዋስትና መሆና ቸው ቀርቶ አሜንቅፋት ናቸው የሚል ነው፡፡ ይህን አቅዋም በመግፋት ድርጅቶች

ን ተከተው መድረክ ሊይዙ የሚቃገፑ ኢምንቶች መኖራቸውም ታይቷል፡፡ ድርጅ ቶች ለድል አያስፈልጉም፤ሕዝቡ በራሱ ንቅናቄ መርቶ ለድል ይደርሳል፤ ድርጅቶ ች እየተከፋፈሉ ችግር ሆነዋል ወዘተ በሚል እየተሰራጨ ያለው ጎጂ ሰበካ የሕዝብ ን ድል የሚጎዳ መሆኑ ከወዲሁ መታወቅ አለበት፡፡ በእርግጥ ድርጅት ነን የሚሉ የሁለት ሶሰት ሰው ስብስቦች መኖራቸው፤ በስደት ዓለም ቢወሰኑም ቅሉ ይህ ነው የሚባል አባል ቁጥር፤ ክብደት ወይም እንቅሰቃሴ የሌላቸው ድርጅት ተብዬዎች መኖራቸው የታወቀ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በሀገርቤትም በውጭም ሚዛን ያለው ስራ የሚሰሩና የሚታገሉ ድርጅቶች እንዳሉ ግልፅ ነው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በሆኑ ምክንያቶች ክፍፍል ቢደርስባቸውም ሚናቸው ሊሰረዝ የሚችል አይደለም፡፡ በእርግጥ የመሪነት ሚናን መጫወት ካቃታቸው ይህ ድክመታቸው በግልፅ ተቀም ጦ የእርምት ሙከራዎች መካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ መከፋፈል ባይፈለግም ሊመጣ የሚችልና የሚመጣ ነውናም ችግሩን እንዳመጣጡና ሚዛኑ መያዝና ለማስወገድም መጣር ይጠበቃል፡፡ ክፍፍል መጣ ብሎ መቆጨቱ ወይም ራስን ለቀቢፀ ተሰፋ ዳርጎ ድርጅቶች አያስፈልጉም ወደሚል መደምድሚያ መድረሱ ስህተት ነው፡፡ ደከም ጠነከር የድርጅት መኖር ጠቀሜታው የሚናቅ አይደለም፡፡

ሕዝብ ካልተደራጀ ሀይሉ አይጠነከርም፡፡ በተባባረ መልክ በስልት ሊታገል የሚችለ ው ከተደራጀ ብቻ ነው፡፡ ከብዙ የድርጅት ተመክሮና የትግል ዓመታት በኋላ ዛሬ ስል ድርጅት አስፈላጊነት ለማውሳት ጊዜ ማጥፋት አስፈላጊ ባልሆነም ነበር፡፡ ዋናው ጉዳይ ወይም ጥያቄ መሆን ያለበትና የነበረበት እንዴት ድርጅቶችን ማጠና ከር እንችላላን የሚል እንጂ ከናካቴው ድርጅትስ ለምን አስፈልጎ የሚል መሆን አልነበረበትም፡፡ ለዚህ ክብደት ሰጥተን የተነሳነው ድርጅቶች አያሹንም የሚሉት የወያኔ የገደል ማሚቴዎች ክብድት ኖሯቸው ሳይሆን በእንጭጩ ይህን ሕዝብን ትጥቅ አስፈቺ ዝንባሌና ሰበካ ውድቅ ለማድረግ ብለን ነው፡፡ ሕዝብ አለመደራጀቱ ጠቀሜታው ለወያኔ ነው፡፡ ምክንያቱም የሕዝብ ከንድ አቅም ያጣል፤ ትግሉ ራሱ ን በራሱ ይጠልፋል፡፡ ግብታዊ ፍንዳታ በትግል ውጤት ላይ የራሱ አሻራ አይኖረ ውም ባይባልም ግብታዊነት ለተደራጀው ጠላት ጠቃሚ ነው፡፡ ወያኔን እንደ ምሳሌ ብንወስድ የራሱ የወያኔ የፖለቲካ ድርጅት አለው፡፡ጦር አለው፤የፖሊስ ሰራ ዊትና የአፈና ተቋሞች የተደራጁ አሉት፡፡ ይህን የተደራጀና አረመኔ የሆነ ጠላት ድርጅት አልባ ሰለባ ልንሆነው መነሳት በራስ ላይ ሞትን መፍረድ ነው፡፡ ይህን

የሚመክሩ ወይም ሕዝብን አትደራጅ ብለው የሚሰብኩ ወይም ድርጅቶች አያስፈልጉህም ብለው የሚለፍፉ በምንም ዓይነት የሕዝብ ወዳጆች ተብለው ሊወሰዱ አይገባም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ወደፊት መግፋት የቻለው በድርጅቶች ስለተመራ ነው:: በድርጅቶች ወይም መሪ ድርጅት አማካኝነት ተግሉን ሊያካሂድ ባልቻለበት ድሉን ተነጥቋል:: ወያኔ በዚህም በዚያም ቢሆን ለድል የበቃው ተደራጅቶ ነው:: በስልጣን ያለውም ባለው ድርጅት በመጠቀም ነው:: መንግሰት ተብዬው ተቋሙ ራሱን የቻለና የማይናቅ ድርጅቱ ነው:: ይህን መዘንጋት ጎጂ ስህተት ይሆንብናል:: ያፍን በታል፤ይደልልበታል፤ ለስርቆትና ሙሰና ይጠቀምበታል:: የሀገርና የሕዝብ ጠላቶ ች ተደራጅተው ወይም ሊደራጁና ሊጠናከሩ ግራ ቀኝ ሲሉ እያየን ለሐዝብ ግን ድርጅቶችን በጠላትነት ፈርጀህ በራስህ ታገል ብሎ አጥፊ ግብታዊነትን መስበክ የሚያስወገዝ ነው:: ሕዝብን ለጠላት አጋፍጦ የሚሰጥ አቅዋም ነው:: ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ዓይነትን ወያኔያዊ ሰበካ ጆሮ የማይሰጠው:: እንዲያውም ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ መደራጀትና ለትግል መነሳት አለበት:: ይህን ለማረጋገጥ ሲነሳም በአንድ በኩል ሀሳዊ መሲህ የወያኔ አዋቂም አላዋቂም ደጋፊዎችን ወደ ጎን ትቶና ጆሮ ነስቶ በሌላ በኩል ግን ድርጀቶችን ለማጠናከር አሰፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ያሻል:: በሀገር ወዳድ ድርጀቶች ላይ የመጣው የአንጃና ከፋፋይ ዶፍ የተገታ ቢሆንም ጉዳት ያደረሰና ሊያደርስም እየተፍጨረጨ ረ ያለ ነውና ሕዝብ ገልተኛ ሳይሆን ጎራውን ለይቶ ለሀገር ወዳዶቹ ድርጅቶ ሙሉ ድጋፉን መስጠት ይጠበቅበታል:: መደራጀት ወሳኝ ነው:: ያልተደራጀ ሕዝብ ለጠ ላቱ ራሱን አጋልጦ ይሰጣል:: ድርጅት ሀየል ነው፤ ድርጅት የትግል ወሳኝ መሳሪያ ነው፤ ድርጅት ምትክ የለሽ ነው:: ድርጅት ስንልም ሕዝባዊና ለሀገር በሀቅ የቆመውን ነው:: የትግል ተመክሮአችን ምን ዓይነት ድርጅት፤ምን ዓይነት ህብረት ወይም ቅንጅት እንደሚያስፈልገን አሳይቶናል:: ባለፈው ትግላችን ያገኘነው ድል በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ድርጅት አያስፈልገንም የሚሉት ሁሉ የቅርቡን የግንቦት 97ን ትግል ሁሉ የሚሰርዙ ናቸው:: ተመክሮ ግን የታለፈውን ደጉንም ድክመቱንም ያሳየናልና የሚታረመውን አርመን በተጠናከረ መልከ ተደራጅትን ትግላችንን እንቀጥል::